የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር
(ኢ.ብአአግ)

Ethiopian National United Patriotic Front
(ENUPF)

# በሥልጣን ለመቆየት የሚደረግ ማምታታትን አጥብቀን እንቃወማለን!

July 28, 2006

መለስ ዜናዊ በሥልጣን ለመቆየት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያልፈጸመውና የማይፈጽመው ወንጀል የለም። አገር አስገንጥሎ መሸጥ፥ ማሸበርና መፍጀት፥ በጐሰኝነትና በጐጥ ከፋፍሎ ሰላምን ማሳጣት፥ የሕዝብን ድምፅ መስረቅና መቅጠፍ፥ የሕዝብን ተወካዮችንና መሪዎችን ሰብስቦ ማሰር፥ የሐገሪቱን ሐብት ዘርፎ በውጭ አገር ባንኮች ማሸሽ፥ የጐረቤት አገሮችን ሰላም መንሳትና የወሰን ጦርነት በመቀስቀስ ሠራዊቱን በጦርነት እሳት መማገድ፥ ለወደፊቱም ትውልድ የጐረቤት ጠላትን ፈጥሮ ለማቆየት መጣር፥ ኢትዮጵያ ሰው አልባ እንድትሆን ብቻ ሳይሆን የማይበርድ ጥላቻን ለትውልድ ማውረስ፥ እንዲሁም የፖለቲካ ሽንፈቱንና ተቃዋሚ አርበኞችን እንቅስቃሴ በመፍራት....

1. የአክራሪ እስላሞችን እንቅስቃሴና መስፋፋትን ለመግታት በሚል ሰበብ ኃያላን መንግሥታትን እያታለለ ብዙ ዕርዳታ ለማግኘት እየጣረ ነው።
2. በአገር ውስጥ አርበኛው የሞት ሽረት ፍልሚያ በማድረግ የሕዝብን እያደራጀ ከየአቅጣጫው ጦርነቱን በተያያዘበት ወቅት ከኤርትራ የተነሳ የተቃዋሚ ድርጅት ወገን በማሰኘት የሠራዊቱን መንፈስ ለመሸንገል ሞመከሩና፥
3. ከውጭ ጠላት ተነሳብን በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሐገር ወዳድ ስሜቱን ለመሳብና ለማደናገር በማያገባው በሶማሌ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የሚያካሂደው የጐረቤት አገር ጦርነትን የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር አጥብቆ ይቃወማል።

የወያኔ ሠራዊት ሆይ! መሪዎችህ የምዕራባዊያን የዕርዳታ ገንዘብ ለማግኘት ብለውና ሥልጣናቸውን ለመቆየት በሚያደርጉት የተንኰል ወጥመድ ውስጥ እየገባህ የኢትዮጵያ ዋና ጠላት ለሆነው ለመለስ ዜናዊ የውንብድና ድርጅት መስዋዕት ከመሆን በመቆጠብ ወገንህ ከሆነው የኢትዮጵያ አርበኞች ጐን እንድትሰለፍ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።
ኢትዮጵያ ነጻነቷን ጠብቃ ለዘለዓለም ትኖራለች!

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር ማዕከላዊ ኰሚቴ።

ENUPF Development Foundation
North America Headquarters
P. O. Box 984, Tucker, GA 30085 • U.S.A. •
Tel. (404) 394-4321 • Fax (770) 414-0061
www.enupfforethiopia.org